የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ምእመናን

ዓለም አቀፍ ማሕበር

4002 Blacksmith Drive, Garland, TX 75044 - www.eotcipc.org

ታሕሣሥ 1 ቀን 2003 ዓ/ም

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።

# መግለጫ

**ጉዳዩ፤** ከጥቅምት 12 እስከ ጥቅምት 20 ቀን 2003 ዓ/ም ስለ ተከናወነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ፤

ማሕበራችን ስለ ቅዱስ ሲኖዶሱ ጉባኤ ውጤት ለማግኘት የቻለውን ግንዛቤ ከተመለከተ በኋላ፤

1ኛ/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስን የ1991 ዓ/ም ሕገ ቤተ ክርስቲያን በጥልቀት ተመልክቶ፤

2ኛ/ ማሕበራችን፤ ከሕዳር 14 እስከ 16 ቀኖች 1999 ዓ/ም ጉባኤውን ካከናወነ በኋላ ያወጣውን የአቋም መግለጫ በማስታወስ (ዝርዝሩን በ www.eotcipc.org ይመልከቱ)፤

3ኛ/ መስከረም 18 ቀን 2002 ዓ/ም ለቅዱስ ሲኖዶሱ "በቤተ ክርስቲያናችን ሰላም፤ አንድነትና ዘላቂ እድገት እንዲገኝ ስለ ማድረግ" በተሰኘ አርእስት ያቀረበውን የመማጸኛ ደብዳቤ በማስታወስ፤ (ደብዳቤውን በwww.eotcipc.org ማየት ይቻላል)፤

4ኛ/ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ተጋርጠው የሚገኙትን ከባድ ችግሮች ለማስወገድ የሚያስፈልጉትን መሠረታዊ መርሆዎች በማጤን፤

5ኛ/ ለቅዱስ ሲኖዶሱ፤ ለቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት፤ ለቤተ ክሕነት መምሪያ እና በአጠቃላይ ለምእመናን በሙሉ ማሕበራችን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሐሳቦች በትሕትና ያቀርባል፤

(ሀ) የቅዱስ ሲኖዶሱ ጉባኤ ከባድ ጉዳዮች ባካተተው አጀንዳ ሙሉ ሕብረት የተንጸባረቀበት ተገቢ የሆነ ውይይት አከናውኖ ለቤተ ክርስቲያናችን ላሁኑም ጊዜ ሆነ ለዘለቄታው የሚጠቅሙ ውሳኔዎች በማስተላለፉ ጥልቅ የሆነ ምሥጋናችንን በትሕትና እንገልጻለን።

(ለ) ኃላፊነቱ የሚመለከታቸው የቤተ ክርስቲያናችን መሪዎችና አካሎች፤ ማለት፤ ቋሚ ሲኖዶሱ፤ ቅዱስ ፓትሪያርኩና፤ የጠቅላይ ቤተ ክሕነት ጽ/ቤት፤ ቅዱስ ሲኖዶሱ ያስተላለፋቸውን ውሳኔዎች፤ ተገቢ የሆነ ስልትና ፕሮግራም በማውጣት ተግባራዊ እንዲያደርጉ እንማጸናለን። ይህንኑም ለአባቶችና ለሕዝበ ክርስቲያን

በአስቸኳይ በመግለጽ ቤተ ክርስቲያናችን የራሷን ውሳኔዎችና ሕግ የምታከብር መሆኑን በግልጽ ማረጋገጥ እንደሚችሉ ጽኑ ተስፋችንን በትሕትና እንገልጻለን።

(ሐ) ከላይ፤ በ1ኛ ተራ ቁጥር በተመለከተው ሕገ ቤተ ክርስቲያን፤ ምእራፍ ሁለት፤ አንቀጽ 5፤ "የቅዱስ ሲኖዶስ ልዕልና/የበላይነት/" በተሰኘ አርእስት፤ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደ ተጻፈው፤

"በመንፈስ ቅዱስ የሚመራው ቅ/ሲኖዶስ የመንበረ ሐዋርያት ወራሽ ስለሆነ በቤተ ክርስቲያኒቱ የመጨረሻው ከፍተኛ ሥልጣን ባለቤት ነው።"

ተብሎ የተደነገገ በመሆኑ፤ ቅዱስ ፓትርያርኩም ሆኑ የበታች እርከኖች የቅዱስ ሲኖዶሱን የበላይነት አክብረው ውሳኔውን በሙሉ ሥራ ላይ እንደሚያውሉ እናምናለን።

(መ) በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የተጋረጡትን ከባድ ችግሮች፤ ለምሳሌ፤ ለአብነት ት/ቤቶች፤ ለገዳሞች፤ ለደብሮች እንዲሁም ስብከተ ወንጌልን በኢትዮጵያና በዓለም-አቀፍ ደረጃ ለማስፋፋትና ለማጠናከር፤ በተጨማሪም አክራሪዎች እያከናወኑ ያሉትን ጥቃት ለመቋቋምና ኢየሩሳሌም የሚገኘው ታሪካዊው ገዳማችን አስፈላጊው ጥገና እንዲከናወንለት ለማድረግ በጥንቃቄና በተሟላ ሁኔታ በተዘጋጀ ስልት፤ በረጅም/የመካከለኛና የአጭር ዘመን ፕሮግራም መንቀሳቀስ እንደሚያስፈልግ እያሳሰብን ለዚሁም ከፍተኛ ዓላማ ማሕበራችን ተባባሪ እንደሚሆን በትሕትና እንገልጻለን።

(ሠ) ከላይ በተራ ቁጥር 2 በተጠቀሰው መግለጫ እንደ ተመለከተው፤ የቤተ ክርስቲያናችንን ከባድ ችግሮች ተቋቁመን ለማስወገድ የሚቻለው፤ ፍቅር፤ አንድነትና ሰላም ሲሰፍን በመሆኑ በልዩ ልዩ ምክንያቶችና ሁኔታዎች የተከሰተው አለመግባባትና መከፋፈል እንዲወገድ በሒደት ላይ የሚገኘውን የእርቅና የሰላም ጥረት በተለይም የሰላምና የአንድነት ኮሚቴውን ተግባር ማሕበራችን ይደግፋል። በዚህ አጋጣሚ፤ ሰላሙንና አንድነቱን በተመለከተ ወደፊት ከማንኛውም ወገን በይፋ የሚወጡትን መግለጫዎች፤ ማሕበራችን በጥንቃቄ እየተመለከተ፤ አቋሙን እንደሚገልጽ እናረጋግጣለን።

(ረ) ቤተ ክርስቲያናችን በሐገር ውስጥና በዓለም-አቀፍ ደረጃ ያለባትን ኃላፊነት በተቀናጀ፤ በቅልጥፍናና በቀጣይነት ለመወጣት እንድትችል አወቃቀሯ ግልጽነትና ጠንካራ የውስጥ አቆጣጠር የሚያስገኝ እንዲሆን እንዲሁም ብቁ የሆነ አመራር እንዲኖራት ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑን እናሳስባለን።

(ሰ) በሚሊዮን የሚቆጠሩት ውጭ ሐገሮች የሚኖሩት ምእመናን፤ በተለይም ወጣቱ ትውልድ እንደ አሸን እየፈላ በመሆኑ፤ የቤተ ክርስቲያናችንም ትምሕርት የሚፈለገውን ያህል እንዲመጥን ሁነኛ ሥፍራዎች እየተመረጡ ብቁ የሆኑ ትምሕርት ቤቶችና ኮሌጆች እንዲቋቋሙ የሚያስፈልግ መሆኑን እናሳስባለን።

(ሸ) ስለ የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔዎች አፈጻጸም ስፊ ግንዛቤ እንዲገኝ ጠቅላይ የቤተ ክሕነት ጽ/ቤት በየሶስት ወሩ በመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት ለምእመናን ገለጻ እንዲያደርግ እናሳስባለን።

ቸሩ አምላካችን ለቤተ ክርስቲያናችን ሰላም፤ አንድነትና፤ ፍቅር እንዲሁም የተፋጠነ ልማትና እድገት ያስገኝልን። አሜን።